# እስቲ እናውራ ካልን፣
# አህያውን ትቶ አይሁን ዳውላውን፣
# ከልብ ካለቀሱ ዕንባ አይገድም በሉን ! 1)

የካቲት 2005

ኢህኣዴግ ሥልጣን ከያዘ 21 ዓመታት አለፈው። የተቃዋሚዎችም ትግል እንደዚሁ፤ ለለውጥ መታገል ከጀመሩ 21 ዓመታት ሆናቸው። ኢህአዴግን ከሥልጣን ለማባረር፣ ኢህአዴግን ያለ ዕረፍት ሲኮንኑ፣ ሲያወግዙ፣ ኧረ ምኑ ቅጡ፤ እውን፣ ሶስተኛውን አስርተ ዓመት ተያይዘነዋል! ኢህአዴግን ለሥልጣን ኮትኩተው ያሳደጉት የባዕድ ሃይሎችም፣ አንዳንዴ መንገዳቸው ጎርበጥበጥ እያለባቸው ቢንፈራገጡም፣ እስከዛሬ ድረስ ጠበበን ደከመን ሳይሉ ተሸክመውት፣ በወዳጅነት ቆይተዋል።

በዚህ ጊዜ ውስጥ ኢህአዴግ በሥልጣኑ ኣደጋ ላይ የወደቀ የመሰለው ለመጀመሪያ ጊዜ በ 1997 ዓ ም/ 2005፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ባደባባይና በምርጫ እንደማይፈልገው በገለጸበት ጊዜ ብቻ ነው። ኢህኣዴግ ዛሬ መሪም የለው፣ ቢሆንም ግን የኢትየጵያ አብዛኛው ህዝብ፣ መንግሥትን ለዘመናት ተቀብሎ መኖር ለምዷልና ያለ መሪም /ወይንም በእጅ፥አዙር ስውር መሪ እንበል/ መኖር መቻሉን ሰሞኑን እያሳየን ነው (የሙዝሊም ወገኖቻችንን ትግል፣ በሆዳችን ይዘን) ! 1997 ዓ ም/ 2005 የኢህአዴግን ሥልጣን የተፈታተነው የለውጥ ማዕበል ለምን ከሸፈ የሚለውን መቼም አንስቶ ብዙ ማውራት፥ መተንተን ይቻላል።

እዚህ የተነሳነው ግን ዋናው፣ ያህያውንና የዳውላውን ምስጢረ ስላሴ ለመፍታት ስለሆነ እንቀጥል።

**ኧረ ለመሆኑ ማነው አህያው፣ ማነው ዳውላውስ ?**
**አህያውን ትቶስ፣ ዳውላውን የሚመታው ለመሆኑ የትኛው የዋሁ ነው?**
**ወይስ ደንቁሮ ወይስ ተሳስቶ ?**
**የሃገራችን የሥልጣን ባለቤት የሆኑት እነማን እንደሆኑ፣ እንዴትስ እንደመጡ ሳያስተውል ቀርቶ፣**
**ወይስ የተንኮለኞች ሰለባ ሆኖ፣ ወይስ ማን አሳስቶት?**

*

እንደሚታወቀው፣ ዳውላው 21 ዓመት ሲወገዝ ሲኮነን፣ ሲተኖኮስ፣ በዱላም፣ በነፍጥም፣ በሰላም፣ በነገርና ባፍም፣ የፕሮፓጋንዳ መዓት፥ዓይነቱ ፣ ምንም አልቀረም። አህያው ከነዳውላው ግን፣ ፍንክች ያባ ቢለዋ ልጅ፣ ፈቅም አላለ! ብዙ ትንተና / የትግል መመሪያ ዲስኩሩና ትምህርቱ ሁሉ፣ 21 ዓመታት ሙሉ ምንም አልቀረም ፣ ሁሉም በየፊናው „አስተምሮናል“ ። ስለዚህ እዚህ ቢደገም፥ቢነዛ፣ ቢደጋገም ማን ነኝ ለማለት ስለሚሆን ተትቷል።

## ስለዚህ አንድ ሁለት ጥያቄዎች ብቻ ቢቀርቡ ይበቃል፤ ቀላል ጥያቄዎች !

ከልብ ካለቀሱ ዕንባ አይገድ ይሉ፣ እነዚህን ጥያቄዎች መመለስ ማንም አያቅተውም።
ያውም 21 ዓመት ሙሉ፣ በፖለቲካ ተቃውሞ ትግል የሰለጠነ፣ ተማርኩ ተመራመርኩ የሚል „መደብ“ !

### ጥያቄ አንድ፥

ካህያውና ዳውላው ተረት ሳንወጣ፣ ኧረ ለመሆኑ ባገራችን የፖለቲካ ኳስ ጨዋታ፣
ዳውላውን ባህያው ጭኖ የሚያዋክበንና የሚያተራምሰን ማን ነው?

### ጥያቄ ሁለት፥

አህያው ማን ነው? ዳውላውስ ?
ይህች አህያ ስንት ዓመት ዳውላውን ተሸክማ ባለበት ብትረግጥም፣ አንዳንዴም ሌላ ቦታ ደረስ ብትልም፣ የታየችበት ቦታ ሁሉ ደህና መስተንግዶ እየተደረገላት ይህን ሁሉ ዓመት ዳውላውን ለምን ተሸክማ ቆየች ?

### ጥያቄ ሶስት፥

አህያዋ የተሸከመችው ዳውላ ውስጥ 21 ዓመት ሙሉ በርሷ ሸክም ሲንከራተት የቆየው እህል ስለበሰበሰ፣ ምን ማድረግ ይቻላል ?
ዳውላ ተፈጥሮው ሆኖ በራሱ አይሄድ፥ አይመጣ ፥ አይወርድ ነገር !

## ጥያቄ አራት፥

አህያዋ ከነዳውላዋ ካለችበት ነቅነቅ ላለማለት፣ እምቢ አሻፈረኝ ስትል፤
አህያዋ ላይ ሌላ ዳውላ ወይ ለመጫን፣ ወይንም አህያዋን ትቶ ሲሆን በወግ ማዕረግ በፈረስ ላይ ወጥቶ
እራስ ለመጋለብ ምን ማድረግ ይቻላል?

*

***ለነዚህ ጥያቄዎች ከኢትዮጵያ ፖለቲከኞች እስከአሁን 21 ዓመት ሙሉ የተገኙት መልሶች በሁለት ይከፈላሉ፥***

# ለጥያቄ አንድ፣

አብዛኛው የደረሰበት ቁም ነገር፣ ድንቁርናና ተንኮል መሆኑን ሲሆን፤

# ለሌሎቹ ሶስት ጥያቄዎች፣

ዳውላው ማን? አህያውም ማን እንደሆን የተሸሸገበት ባይኖርም፣
አህያዋ ስትለግምና ስትራገጥ፣ ሁኔታውን ለመቀየር ዘዴው አወዛጋቢ ሆኗል፤

ባለፉት 21 ዓመታት የታዩትን ከንውኖች እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል፥

## አንደኛው ወገን፥

በብዛት ዛሬ ድረስ የተደረገውና ሥራ ላይ የዋለው፣ ጉልበትን ለነግ ሳይሉ፣ ህመሙ አህያው ላይ እስቲደርስ ደረስ፣
ዳውላውን መደብደብ / በተለያየ ዘዴ !! ሲያስፈልግ በሰላም፣ ሲያቅት በህግ አምላክ፣ ያም ሳይሆን በህገ ወጥ፣ በነፍጥ፣
በሰደፍ መደብደብ! ነው ሲል፣

## ሁለተኛው ወገን ደግሞ ፣

በሚፈራ፣ በሚቸርና በጣም በዝቅተኛ፣ድምጽ፣
ዳውላውን ትቶ አህያውን በቅጡ መደብደብ፣ ያኔ አህያው ዳውላውን ጥሎ ይሄዳል ወይንም ድብደባው ሲበዛበት፣
ተፈራግጦ 21 ዓመት የበሰበሰ ዳውላውን ጥሎ፣ በሌላ ዳውላ ይጫናል፣ ከልሆነለትም ለፈረስ መንገድ ይለቃል፣
ሲል ይሰማል።

## በዚህም፣ ዋናው፣ የመደምደሚያ ጥያቄም ሆኖ ያፈጠጠው
## ጥያቄ አንድ
## ሆኗል፥

***መቼ ይሆን አብዛኛው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ተዋናይ ከድንቁርና ና ተንኮል ተላቆ፣ የደነዘዘው ዳውላው ላይ ከመውረድ ይልቅ፣ እስካሁን የፈራው፣ አህያው ላይ ወርዶበት፤ ይህን አህያ፣ ወይ በአዲስ የሚጭነው፣ ወይንም ሲሆን፣ በወግ ማዕረግ እንደሰው ፈረስ ግልቢያ የሚማረው !!??***

*

# ኢትዮጵያ ከአዲሱ እጅ አዙር አገዛዝ ነጻ ትውጣ!
# ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

*

*1) ኢትዮጵያን ዛሬ ማን ነው የሚያስተዳድራት ? ኢህአዴግ በአሜሪካና በምእራብ አውሮፓ፣ አንድ ምሁር እንዳሉት፣ በሚተነፍሰው ኦክሲጂን ካልተደገፈ አንድ ቀን ኣያድርም። ግፋ ቢል የቻይና ጉያ ውስጥ ገብቶ ይለይለታል። ያኔ ደግሞ ቻይናን የማይወዷት እዚሁ አካባቢ ጉድ ጉድ ማለታቸው አይቀርም! ይህ ሆኖ ሳለ ፣ በተለይ ከውጭ ሆነው ኢህአዴግን የሚታገሉት የፖለቲካ ሃይሎች ዋናው ትግላቸው ፣ ኢህአዴግን በህይወት የሚያቆዩት እነዚህ ሃይሎች ላይ ለምን እንደማያተኩር በመገረም የተፈለገ ምሳሌ ነው።* ***„አህያውን ፈርቶ ዳውላውን !“***
*እንዳው ለምሳሌ ያህል፣ ሰሞኑን ካራቱሪ የሚባለውን በሃገራችን መሬት ከተስፋፉት የባእድ ባለጸጎች ውስጥ አንዱ፣ የሚፈጽመውን በደል ለማጋለጥ የማደንቀው የነጻነት ታጋይ ኦባንግ ሜቶ ይህ እንዴት እንደሚደረግ፣ አሳይቶናል። ውጤት የሚሰጥ የዚህ ዓይነት የማያቋርጥ ዘመቻ እንዴት እንደሚደረግ ደግሞ ብዙ ሌሎች ልምዶችም አሉ ? ኢህአዴግን ለመታገል ሁሉም በየፊናው ብዙ ጉልበትና ሃይል ያፈሳል። ኢህኣዴግ ከወዳጆቹ የሚተነፍሰው አየር እንዳያገኝ ስር የሰደደና የተቀላጠፈ ዘመቻ ከማድረግ ተቃዋሚ ሃይሎችን፣ /በተለይ የዲያስፖራውን / 21 ዓመት ሙሉ ግን፣ ምን ሲያግዳቸው እንደቆየ አይገባኝም! ችግሩ ድንቁርና ይሁን ሌላ፣ ወይስ አሻንጉሊትነት፣ ስላልገባኝ፣ ሃገር ወዳድ ነኝ የሚል ሁሉ ከራሱ አዕምሮ ጋር ይነጋገር ዘንድ የመጣ ሃሳብ ነው! ሕ. ብ.*